# የተጀመረው የለውጥ  ዕርምጃ ተጠናክሮ ይቀጥል!!

## *በአውሮፓ የኢትዮጵያውያን ኮሚንቲዎችና የሲቪክ ማህበራት የጋራ መግለጫ*

ኢህአዴግ አገሪቱን ላለፉት ሀያ ሰባት ዓመታት የአንድ ፓርቲ ስርአራት ዘርግቶ ሲገዛ መቆየቱ  የሚታወቅ ነው። የአገዛዝ ስርአቱን ለማስረጽና ቀጣይነቱን ለማረጋገጥም የተቃወሙትን ሁሉ አስሯል፣ አሰቃይቷል አሰድዷል፣ገድሏልም። የመንግስት ግፍና በደል ግን ከቶውንም ምልዓአተ ህዝቡን ለበለጠ ትግልና አመጽ አስነሳ እንጂ፣ አላበረደውም። በተለይ ባለፉት ሶስት ዓመታት የታየው የህዝቦች ትግልና አመጽ፣ በአንድ በኩል የኢሃአዴግን ሽንፈት አይቀሬነት ሲያረጋግጥ፣ በሌላ በኩል ግን የአገሪቱን አንድነትና ቀጣይነትም አሳሳቢ አድርጎት ነበር።

የኢትዮጵያ ህዝቦች ትግል ማየል፣ በራሱ በኢህአዴግ ውስጥም፣ ትግል እንዲደረግና ከህዝብ የወገኑ ሀይሎች ጎልብተው እንዲወጡ የረዳ ሲሆን፣ ይህም እንደ አቶ ለማ መገርሳ፣ አቶ ገዱ አንዳርጋቸውና ዶክተር አብይ አህመድ የመሳሰሉ የለውጥ አራማጆች ወደፊት እንዲመጡና ስልጣንም እንዲይዙ አድርጓል።

አዲሶቹ የኢህአዴግ የለውጥ ሀይሎች ምንም እንኳ ከገዥው ፓርቲ የወጡ መሆናቸው ቢታወቅም፣ መንግስታቸው ባለፉት አመታት በህዝቡ ላይ የፈጸመውን በደል በማመን ይቅርታ ጠይቀዋል። የህዝቡን ሰብአዊ መብቶች በማክበርና በማስከበር የአገሪቱን አንድነት ጠብቀው ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመገንባት፣ ከሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር ሁሉ ለመስራት ዝግጁ መሆናቸውንም እየገለጹ ነው። አንድም የፖለቲካ እስረኛ የለም ይባልባት በነበረችው ኢትዮጵያ፣ ከሁለት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ከ60 ሺ በላይ እስረኖች መፍታታቸው አገሪቱ ምን ያህል የዜጎቿ እስርቤት እንደነበረች ብቻ ሳይሆን፣ የአዲሶቹን አመራሮች የለውጥ ፍላጎትና ቁርጠኝነትም የሚያሳይ ሁኗል።

ዶክተር አቢይ አህመድ፣ በሚያደርጓቸው ንግግሮች፣ ባለፉት አመታት በአገሪቱ ውስጥ የተዘራው የጥላቻ ስሜትና የመለያያ ግምብ እንዲፈርስና፣ ባንጻሩ፣ በህዝቦች መካከል የወንድማማችነትና የአንድነት ስሜት እንዲዳብር ረድቷል፣ እየረዳም ነው። በዚህም ምክንያት ዛሬ ከሁለት ወራት በፊት በአገሪቱ ላይ አንዣቦ የነበረው አደጋ ተገፎ፣ በመላ አገሪቱ የተስፋ ጮር ፈንጥቆ ይታያል።

ይህ ሁሉ ግን በአገሪቱ የደረሰውን ቀውስና ችግር ለማስወገድ የሚያስችሉ ጅምሮች ስለታዩ እንጂ፣ መሰረታዊዎቹ የህዝብ ጥያቄዎች ስለተመለሱ ወይም ችግሮቹ ስለተወገዱ አይደለም።በመሆኑም ዶክተር አቢይ የሚመሩት የለውጥ ሀይል ቃል የገባባቸውን የፖለቲካ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን በመተግበር ለአገሪቱ ፖለቲካዊና  ኢክኖሚያዊ ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ ለማምጣት ገና በርካታ ወሳኝ እርምጃዎችን መውሰድ የሚጠበቅበት ሲሆን፣ በእስካሁኑ እርምጃዎቹ ግን ሊበረታታና ሊደገፍ እንደሚገባው እናምናለን።

በመሆኑም  እኛ ከዚህ በታች ስማችን የተጠቀሰው በአውሮፓ የተለያዩ አገሮችና ከተሞች የምንገኝ የኮሚኒቲ ስብሰቦች፣ የሲቪክና የሙያ ማህበራት ድጋፍ ሰጭ ኮሚቴዎች፣ በዶክተር አቢይ የሚመራው የኢሃአዴግ የለውጥ ሀይል የወሰዳቸውን እና እየወሰዳቸው ያሉትን እርምጃዎች እያደነቅን፣  የአገሪቱን የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ችግሮች በዘላቂነትና ዴሞክራሲያዊ አግባብ ለመፍታት የሚያደርገውን ጥረት በሙሉ ልብ የምንደግፍ መሆኑን እናስታውቃለን።

በአንጻሩ የህዝባዊ ወያኔ ሀርነት ትግራይ (ህውሀት) ማእከላዊ ኮሚቴ፣ ዶክተር  አብይ እየወሰዳቸው ያሉትን የማሻሻያ እምርጃዎችንና የእስረኞችን መፈታት ጭምር በመቃወም ያወጣው መግለጫ፣እጅግ በጣም አሳዝኖናል አስቆጥቶናልም። ባለፉት ሀያ ሰባት ዓመታት ህዝቡ ለደረሰበት ስቃይና፣ አገሪቱ ለገባችበት ቀውስ ህወሀት ግምባር ቀደም ተጠያቂ መሆኑ እየታወቀ፣ በፍቅርና በይቅርታ የታጀበ የማሻሻያ እርምጃ እየወሰዱ ያሉትን የለውጥ ሀይሎች ለመገዳደር መሞከሩ፣ ህወሀት ካለፈው ስህተቱ በመማርና እራሱን በማስተካከል የለውጡ አካል ለመሆን ገና ብዙ የሚቀረው መሆኑን የሚያመላክት ነው። በመሆኑም ህወሀትም ሆነ ሌሎች የተጀመረውን የለውጥ ሂደት ለማደናቀፍ  የሚሞክሩ ሀይሎች፣ከድርጊታቸው ታቅበው፣ ከተቻለ የለውጡ አካል እንዲሆኑ፣ ካልሆነ ግን ከአፍራሽ ተልዕኳቸው እንዲቆጠቡ አጥብቀን እናሳስባለን።

### ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!

በቤልጀየም የኢትዮጵያውያን ማህበር
በሆላንድ የኢትዮጵያውያን ማህበር
የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ ማህበር በኢጣልያ
በፈረንሳይ የኢትዮጵያ ማህበር
በስዊድን የኢትዮጵያ ማህበር
በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ድርጅት  (AHRE)
የአፋር ሰብአዊ መብቶች ድርጅት
በአውሮፓ የኢመማ ድጋፍ ኮሚቴ
የኢትዮጵያ ነጻ ጋዜጠኞች ማህበር (EFJA)
ድልድይ፣ በአውሮፓ የኢትዮጵያውያን መድረክ